ሚኒስቴር ጥበብ አ.ማ

ኢትዮ-ፓረንትስ ት/ቤት

የ 2012 ዓ.ም የ 2 ኛው ወሰነ ትምህርት የስነዜጋና ሰነምግባር ትምህርት ማስታወሻ

ምዕራፍ ስምንት

ራስን መቻል(Self-Reliance)

8.1 - የራስን መቻል ምንነትና ጠቀሜታ፡

ራስን መቻል ማለት በራስ ላይ እምነት ማሳደር ማለት ሆኖ በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል::

ለምሣሌ- በግል ህይወት ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ችግሮች በራስ ጥረት

መፍታት

- በራስ ጥረት ኢኮኖሚያዊ ፍላጐቶችን ማሟላት፣

- በራስ ተነሳሽነት ሥራን ጠንክሮ መሥራት፣

- የራስ ፍላጐትና ምርጫ ለማክበር በሌላ ሰው ውሳኔና ፍላጐት አለመመራትና

የራስን መቻል ጠቀሜታ

አንድ ሰው በዕውቀቱ፣በጉልበቱና በኢኮኖሚ አቅም እራሱን ከቻለ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ሀ- የእኩልነት ስሜትና ችሎታን ይፈጥራል።

ለ- ራሱን የቻለና በራሱ የሚተመማን ሰው ውጤታማ ስራን ይሰራል።

ለምሳሌ፡- ትምህርቱን በአግባቡ የሚማር ተማሪ የተሻለ ዕውቀትና ውጤት ይኖረዋል።

ሐ- ሰዎች ከኢኮኖሚ፣ ከአስተሳሰብ እና ከማህበራዊ ጥገኝነት ነፃ እንዲሆኑ ያስችላል።

ለምሣሌ፡- ጊዜውን ተጠቅሞ የሚያጠና ተማሪ ከሌሎች ተማሪዎች ለመኮረጅና ጥገኛ መሆንን

አይፈልግም።

መ- የግለሰብንም ሆነ የሃገር ልማትና ዕድገትን ያፋጥናል።

8.2- ጥገኝነት

ጥገኝነት ማለት ከልክ ባለፈ መልኩ በሌሎች ሰዎች <u>ዕውቀት</u>፣ <u>ጉልበት</u>፣ <u>ገንዘብና</u> በመሳሰሉት ላይ የራስን ፍላጐት ለማሟላት መሞከር ማለት ነው።

በሌሎች ሰዎች ላይ በሰነ ልቦና ወይም በቁሳዊ ነገሮች ጥገኛ ሊሆኑ ይችላሉ።

<u>ለምሣሌ፡</u>- በራስ አስተሳሰብና ችሎታ አለመተማመን።

የጥገኝነት መገለጫዎች፡-

ሀ- የራስ ችሎታንና ዕውቀት አለማወቅ፣

ለምሥሌ፡- የራሱን ችሎታ ያላወቀ ሰው ችሎታውን ለመረዳትና ለማዳበር ይቸገራል።

ለ- በራስ አለመተማመን፣

ለምሣሌ፡- በራሱ የማይተማመን ሰው ሃሳቡን ለመግለጽ ይቸግረዋል። በራሱ ውሳኔዎችን

ለማስተላለፍ አይችልም።

ሐ- የሌሎች ሰዎችን ሃሳብ ብቻ ለመቀበል ይገደዳል። በራሳቸው የማይተማመኑ ሰዎች የራሳቸው የሆነ አቋም አይኖራቸውም፣ ቢኖራቸውም ፀንተው ለመቆየት ይቸገራሉ።

ለምሣሌ፡- ፈተናን ከሌሎቹ ተማሪዎች የሚገለብጥ ተማሪ የራሱ የሆነ እምነትና አቅም

አይኖረውም።

መ- ራስን አለመሆን፡ ጥገኛ የሆነ ሰው እራሱን ዝቅ በማድረግ የበታችነት ስሜት

ይሰማዋል። የራሱን ነፃነት አሳልፎ ይሰጣል።

ለምሣሌ፡- ችግር ፈቺ አለመሆንና ለላቀ ስራ ክብር አለመስጠት ወዘተ ያስከትላል።

ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት

ጥገኝነት በሃገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና በማህበራዊ ትስስር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። ዜጐች በገንዘብ፣ በዕውቀት፣ በአስተሳሰብ እራሳቸውን ካልቻሉ በሃገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ ተጽኖ ያመጣሉ።

ለምሣሌ፡-

ሀ- የኮንትሮባንድ (ህገወጥ ንግድ) እንቅስቃሴ መስፋፋት፣

ለ- ወንጀልነክ ድርጊቶች መበራከትና የስዎች ሠላምና ጤና መታወክ፣

ሐ- የራስን ማንነት (ባህል) መርሳትና የሌሎችን ሀገር ሳይፈልጉ መስተናገድ።

ለምሣሌ፡- ከባህላችን ተፃራሪ የሆኑ አስተሳሰቦችና ልማዶች መስፋፋት።

8.2- በራስ መተማመን

የአንድን ሰው በራስ መተማመን ስሜትን የማያመለክቱ ሁኔታዎች መካከል የሚከተሉት ዋና

ዋናዎቹ ናቸው።

1- በራስ ማንነት መኩራትና ሃሳብን ያለ ፍርሃት መግለጽ።

2- አቅምን ማወቅና ሁኔታዎችን አመዛዝኖ ውሳኔ መስጠት።

3- ከራስ እቅድና ፍላጐት ጋር አብረው የሚሄዱ ጉዳዮችን መምረጥ፣

4- ጠንካራ የስራ ባህልን በማዳበር ከሌሎች ጥገኝነት መላቀቅ።

ለምሣሌ፡- አንድ ተማሪ ግዜውን በእቅድ በመምራት ሁሌ ትምህርቱን ማጥናት ይኖርበታል። በእቅድ የሚመራ ተማሪ ፈተና በደረሰ ጊዜ በራስ መተማመኑ ከፍተኛ ነው። ከሌሎች ለመኮረጅና ጥገኛ ለመሆን ፈጽሞ አያስብም።

በአጠቃላይ በራስ መተማመን ራስን ከመቻል ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። በሌሎች ሰዎች ላይ ጥገኛ ሆኖ የሚኖር ሰው በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ በራሱ የሚተማመን ዜጋ ሊሆን አይችልም ሌላ በኩል ጠንክሮ መስራትን ባህል ያደረግ ሰው ምን ጊዜም በራሱ የመተማመን አቅሙ

ከፍተኛ ነው። የሌሎችን አስተሳሰብ በነፃነት ስለሚያስተናግድ በሌሎች ተጽኖ ስር አይሆንም።

የምዕራፍ ስምንት የክለሳ ጥያቄዎች

I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ትክክለኛ መልስ ስጡ።

1- ራስን መቻል ማለት ምን ማለት ነው?

2- አንድ ሰው ራሱን በመቻሉ ምን አይነት ጥቅሞችን ያገኛል?

3- በስዎች ላይ ጥገኛ ሆኖ መኖር ምን ጉዳት አለው?

4- የጥገኝነት መገለጫ ባህሪያት ምንድናቸው?

5- ጥገኝነት በሃገር ዕድገት ላይ የሚያስከትለውን ጉዳቶች ግለፁ?

6- አንድ ተማሪ በፈተና ጊዜ ከሌሎች ተማሪዎች የፈተናውን መልስ ቢኮርጅ ምን ጉዳት ይኖረዋል?

7- በራስ መተማመን ማለት ምን ማለት ነው?